## የጻድቃን ክብርና አማላጅነት

አማላጅነት ወይም ምልጃ የሚለው ቃል ማማለድ ከሚለው ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ከመካከል ገብቶ በመለመን ጠብን ወይም ጠላትነትን ማስወገድ ማለት ነው።

በዚህ መሠረት የእግዚያብሔር ወዳጆች የእግዚያብሔርን መቅሰፍት ለማስወገድ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል በመሆን ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን ልመና አማላጅነት ይባላል።

**ጥያቄ** - የማማለድ ሥልጣን ያላቸው እነማን ናቸው?

**መልስ** - በመልካም ሥራቸውና በተመሰገነው ሃይማኖታቸው የእግዚአብሔር ወዳጆች የሆኑ ወንዶችም ሴቶችም የማማለድ መብት ተሰጥቶአቸዋል። እነዚህ ወገኖች ቅዱሳን ጻድቃን እየተባሉ ይጠራሉ።

**ጥያቄ** - የዘመኑ የሃይማኖት ተከራካሪዎች ስለ አማላጅነት ምን ይላሉ?

**መልስ** - በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሌላ ሰው ሊገባ አይችልም፣እግዚአብሔርም እንደ ሰው አማላጅነትን አይቀበልም፣ ወይም ፍርዱን በአማላጅ በምንም ኣይነት አይለውጥም፤ ስለዚህ በአማላጅነት ማመን ስሕተት ነው  ይላሉ።

**ጥያቄ** - ዋናው መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነውና ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

**መልስ** - የእግዚአብሔርን ሕግ ለሚያከብሩና በእውነተኛውም እምነት ለጸኑ ሰዎች የማማለድ መብት እንደ ተሰጣቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል። ይህንንም ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

### የአብርሃም አማላጅነት

1ኛ. አብርሃም በእግዚአብሔር ተጠርቶ እግዚአብሔርን ካመነበት ጊዜ ጀምሮ

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ወዳጅ ነበር (ዘፍጥ. ለ2፥ ለ3 - ለ6)። እግዚአብሔርም የአብርሃም አምላክና ወዳጅ ነው። በዚሁ መሠረት ኃጢአትን በየቀኑ መሥራትና ልዩ ልዩ አጸያፊና የረከሰ ነገርን በመፈጸም እግዚአብሔርን ያስቆጡትን የሰዶምንና የገሞራን ሕዝቦች ሊያጠፉቸው ማሰቡን አስቀድሞ ለወዳጅ ለአብርሃም ገለጸለት፣ «እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውረዋለሁን?» ብሎ አስቀድሞ ነገረው(ዘፍጥ.ለ8፥ለ7 ።

አብርሃም ይህንን ባለሙዋልነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ማግኘቱን እንደ ተረዳ የማማለድ ሥራውን ለመጀመር በእግዚአብሔር ፊት እንደ ቆመ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። በዚሁ ዓይነት እግዚአብሔር በሶዶምና በገሞራ ሊያመጣባቸው ያቀደውን መቅሰፍት አብርሃም ለማስቀረት በእግዚአብሔር ፊት በመቆም እግዚአብሔርን አምስት ጊዜ አጥብቆ ማለደ። በእነዚያ ከተሞች «አምሳ ጻድቃን ካሉ፣ ወይም ሠላሳ ጻድቃን ካሉ፣ ወይም ሃያ ጻድቃን ወይም አስር እንኳን ቢኖሩ ጌታ ሆይ ስለ እነዚያ ብለህ እነዚያን ከተሞች አታጥፋቸው» በማለት አብርሃም አጥብቆ ማለደ። ነገር ግን በእነዚያ ከተሞች ከሎጥና ከቤተሰዎቹ ማለት ከስምንት ሰዎች በስተቀር እግዚአብሔርን የሚያምኑና ወደ እግዚአብሔር የሚጸልዩ ሰዎች ስላልተገኙ እግዚአብሔር የአብርሃምን ምልጃ ተቀብሎ ከተሞቹን ሊምራቸው አልፈቀደም (ዘፍጥ.፲፰፥፲፯ - ፴፫)።

በእነዚያ ከተሞች ማለት በሰዶምና በገሞራ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ይኖር ነበር። ነገር ግን ከዚያ ሁሉ ሕዝብ መካከል አብርሃም እንዳለው የመጨረሻውን ቁጥር የያዙ አሥሩ ጻድቃን እንኳን ቢኖሩ ኖሮ እግዚአብሔር በአብርሃም ምልጃ አማካኝነት ከተሞቹን እንደማይደመስስ ገልጾለት ነበር።

2ኛ. የጌራራ ንጉሥ የነበረው አቤሜሌክ የአብርሃምን ሚስት ሣራን ነጥቆ በወሰደ ጊዜ፣ እግዚአብሔር አቤሜሌክን በራእይ ገሰጸው፤ «እነሆ አንተ ስለ ወሰድሃት ሴት ምውት ነህ (ትሞታለህ » አለው (ዘፍጥ. 20፥1 - 7)። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር በአቤሜሌክም ቤት የነበሩትን ሴቶችንና እንስሳትን ሁሉ ማኅጸናቸውን ዘጋ (አደረቀ)። አቤሜሌክ አብርሃምን ጠርቶ ይቅርታ ጠየቀው። እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ አቤሜሌክ ሣራን «ጽድቅሽ ለሰዎች ሁሉ ተገልጦአልና» ብሎ ለአብርሃም መለሰለት። አብርሃም ስለ አቤሜሌክ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም አቤሜሌክን፣ ሚስቱንም፣ አገልጋዪቹንም ሁሉ ፈወሳቸው፣ እነርሱም ወለዱ (ዘፍጥ. ሉ፥ 8 - ለ8 ። ስለዚህ በአብርሃም ምልጃ እግዚአብሄር አቤሜሌክንና ቤተሰዎቹን እንደ ፈወሳቸውና ይቅርታ እንዳደረገላቸው። ተመልክተናል።

በመሠረቱ የዘመኑ ተከራካሪዎች እንደሚሉት ቢሆን ኖሮ፣ አብርሃም በእግዚአብሔርና በአቤሜሌክ መካከል ገብቶ ስለ አቤሜሌክ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ አያስፈገልገውም ነበር። ራሱ አቤሜሌክ ስለ ራሱ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ በቻለ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ለቅዱሳን ወዳጆቹ ያለውን ፍቅር ለመግለጽ የማማለድ መብት ስለ ሰጣቸው፣ በዚህ መሠረት አብርሃም ስለ አቤሜሌክ ወደ እግዚአብሔር ማለደ፣ እግዚአብሔርም ሰማው።

## የሙሴ አማላጅነት

1ኛ. የግብጽን ንጉሥ ፈርኦን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባለመስማቱ እግዚአብሔር ግብጽን በእንቁራሪት [ጉጉንቸሮች] አስወረራት። መላዋ የግብጽ ምድር በእንቁራሪት ተወረረች። ፈርዖን ይህንን አስደንጋጭ መቅሰፍት አይቶ ሙሴንና አሮንን ጠርቶ «ጉጉንቸሮቹ ከእኔን ከሕዝቤም እንዲርቁ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ» አላቸው። ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ (አማለደ) ፤ እግዚአብሔርም በሙሴ ምልጃ ጉጉንቸሮቹን በሙሉ ገደለ (ዘጸአ.8፥8 - 15)።

2ኛ. ቀጥሎም ግብጽን ተናካሽ የዝንብ መንጋ በወረራት ጊዜ ፈርያን ዳግመኛ ሙሴንና አሮንን ጠርቶ «ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ» አላቸው። በዚህ ጊዜ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ (አማለደ) የዝንቡ መንጋም በሙሴ ጸሎት ተወገደ (ዘጸአ. 8፥25 - 31)።

3ኛ. እስራኤላውያን ጣኦትን በማምለክ ከባድ ኃጢአት በፈጸሙ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን ጠርቶ «ይህንን ሕዝብ አጠፋለሁ፤ (እደመስሳለሁ)፤ አንተንም በታላቅ ሕዝብ ላይ እሾምሃለሁ» ባለው ጊዜ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር አጥብቆ ጸለየ፤ (አማለደ)፤ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በሙሴ ምልጃ ሊያደርገው ካሰበው መቅሰፍት ተመለሰ፤ መቅሰፍቱን አስቀረ፤ ሕዝቡንም በሙሴ ጸሎት ይቅር አለ (ዘጸአ. ሊ2፥ለ1 - ለ4)።

4ኛ. ሙሴ ኢትዩጵያዊትዋን በማግባቱ ወንድሙ አሮንና እታቱ ማርያም ሙሴን ተቃወሙት። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር የነገሩ ጀማሪ የነበረችውን ማርያምን በለምጽ በሽታ መታት። ነገር ግን ሙሴ ሰባት ቀን ወደ እግዚአብሔር ጸለየላት፤ እስዋም ሰባት ቀን ቤት ተዘግቶባት ስትጸልይ ሰነበተች። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር በሙሴ ጸሎት ፈወሳት (ዘኁል. 12፥1-7)።

## የነቢየ እግዚአብሔር አማላጅነት

ስሙ በውል ያልተጠቀሰ የእግዚአብሔር ሰው በሚል ቃል የተጠቀሰው ሰው ዕጣን እያጠነ በነበረው በንጉሡ በኢዮርብዓም ላይና በመሠዊያው ላይ ትንቢት ተናገረ። ንጉሡም እጁን ዘርግቶ «ያን ሰው ያዙት» ብሎ አዘዘ። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ሰው በተናገረው ትንቢት መሠረት የንጉሱ እጅ ደረቀች። እንደ ተዘረጋችም ቀረች፤ ሊያጥፉት ቢሞክርም አልቻለም። ስለዚህ «የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ የደረቀችው እጄ ትመለስ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ» አለው። ያም የእግዚአብሔር ሰው ወደ እግዚአብሔር ለመነ፣ ወዲያው የደረቀችው የንጉሱ እጅ ወደ እርሱ ተመለሰችለት፣ ማለት ታጠፈችለት፣ እንደ በፊቱም ሆነችለት (1ነገሰ. 13 1-7)።

## የነቢዩ ኤልያስ አማላጅነት

ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ በጸሎቱ ብዙ አስደናቂ ተአምራት ፈጽሞአል። ከእነሱም መካከል

1ኛ. እግዚአብሔርን የተው ወገኖችን ለመቅጣት ዝናብ እንዳይዘንብ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፣ ዝናብም በኤልያስ ቃል ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ጠፋ፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከእነዚያ ዓመታት በታላ ነቢዩ ኤልያስ ዝናብ እንዲዘንብ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፣ ዝናብም በሚገባ ዘነበ (1ነገስ.17፥1-7 እንደገና 1ነገስ. 18፥30-46)።

2ኛ. ለሞተው ልጅ ስለ እናቱ ነቢዩ ኤልያስ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፣ የልጁም ነፍስ ተመለሰችለት ልጁም ከሞት ተነሳ (1ነገስ. 17 17-24)።

ገባሬ ተአምር ኤልሳዕ በጸሎቱ ብዙ ተአምራት አድርጎአል። ከእነዚህም ተአምራት መካከል አንደኛመው የሞተውን ልጅ ጸልዮ ማስነሣት ነው። ነቢዩ ኤልሳዕ ታሞ የሞተውን የመበለትዋን ልጅ ው እግዚአብሔር ጸልዮ ከሞት አስነሣው፣ ለእናትዮዋም ሰጣት ( ነገሥ. ፬፥፲፰-፴፯□።

## የጻድቁ የኢዮብ አማላጅነት

ሦስቱ የኢዮብ ወዳጆች ባካሄዳቸው በአነጋገራቸው እግዚአብሔርን አሳዘኑ። ስለዚህም እግዚአብሔር እንዲህ አላቸው፤ «ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ዘንድ ሂዱ፤ የሚቃጠለውንም መሥዋእት ስለራሳችሁ አሳርጉ፤ ባሪያዬ ኢዮብም ስለ እናንተ ይጸልያል...» አላቸው። ኢዮብም እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ስለ እነሱ ጸለየ፤ እግዚአብሔርም የኢዮብን ፊት [ጸሎት] ተቀበለ (ኢዮብ 42፥7-10)።

## የዳዊትና ኤርምያስ አማላጅነት

በዚሁ መሠረት እነ ዳዊት ስለ ሕዝባቸው ጸሎትና መሥዋእት ለእግዚአብሔር በማቅረብ መቅሰፍት(በሽታ) እንዲወገድ እንዳደረጉ (2ሳሙ.24፥15-25) እንደዚሁም ሙሴና ሳሙኤል የማማለድ ሥልጣን እንደ ተሰጣቸው የመሰከረው ነቢዩ ኤርምያስ (ኤር.15፥1)፣ ሕዘበ እስራኤልን ወደ እግዚአብሔር በጸሎት እንዲያማልድ፣ ምህረት እንዲጠይቅላቸው የእስራኤል ልጆች ደጋግመው በጠየቁት መሠረት የምልጃውን ጸሎት እንዳደረገላቸው ያስረዳናል። ሕዝበ እስራኤል ነቢዩ ኤርምያስን «እባክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን» አሉት። ከአሥር ቀንም በኋላ ነቢዩ ኤርምያስ ሕዝቡን ሰብስቦ እንዲህ አላቸው «ጸሎታችሁን በፊቱ (በእግዚአብሔር ፊት) አቀርብ ዘንድ ወደ እርሱ የላካችሁኝ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል - ስላደረግሁባችሁ ክፉ ነገር ተጸጽቻለሁና በዚህች ምድር ብትቀመጡ እሰራችኋለሁ እንጂ አላፈርሳችሁም፤ እተክላችታለሁ እንጂ አልነቅላችሁም» አላቸው (ኤር.42፥1-17)።

## የአማላጅነት አገልግሎት በዘመነ ሀዲስ

በዘመነ ኦሪትና በዘመነ ነቢያት የነበሩ ቅዱሳን ሰዎች የማማለድ አገልግሎት ይፈጽሙ እንደ ነበር ከዚህ በላይ በአጭሩ ተመልክተናል። ይህ የአማላጅነት አገልግሎት ሳያቋርጥ በዘመነ ሐዲስም ማለት ጌታችን በምድር ላይ በነበረበት ዘመንና በዘመነ ሐዋርያትም ይሠራበት እንደ ነበር ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

በወንጌል እንደ ተጻፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ ሰዎች «ልጄ ታሞ ሊሞት ተቃርቦ አልና መጥተህ ፈውስልኝ! የምወደው አገልጋዬ እጅግ ታሞአልን መጥተህ ፈውስልኝ!..» እያሉ ሲለምኑት ልመናቸውን እየሰማ በመሄድ ይፈውስላቸው ነበር። ለምሳሌ አንድ መጀንን (አንድ ባለሥልጣን) ልጄ አሁን ሞተች፤ ነገር ግን መጥተህ እጅህን ጫንባት፤ በሕይወትም ትኖራለች (ሕይወትንም ታገኛለች) እያለ እየሰገደ በለመነው ጊዜ ጌታችን ሄዶ የሞተችውን ልጁን ከሞት እንዳስነሳነት እንመለከታለን (ማቴ. 9፥ለ8-ሉ5)። በዚህ ዓይነት ጌታችንን እየለመኑ ልጆቻቸውን ያስፈወሱ ብዙ ናቸው (ማቴ.15፥21፤ 17፥14፤ ማር. 5፥22-44)።

እንደዚሁም ከዕለታት አንድ ቀን የአይሁድ ሽማግሌዎች ወደ ጌታችን መጥተው የመቶ አለቃውን አገልጋይ ሄዶ እንዲፈውስለት አጥብቀው ስለማለዱት ልመናቸውን ተቀብሎ እንደሄደ ቅዱስ ሉቃስ ያስረዳ ናል (ሉቃ. 7፥1-10)።

ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንዳንድ ጊዜ በሽተኞቹ በቀጥታ ሲለምኑት ይፈውሳቸው እንደ ነበረ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከዚህ በላይ እንዳየነው ስለ በሽተኞቹ ሌሎች ጌታችንን እየለመኑ ያስምሩአቸ ው ነበር። በዚሁ መሠረት አማላጅነት ማለት አንዱ ስለሌላው ሆኖ መጸለይና ማስተማር ማለት ነው።

## አማላጅነት በሀዋርያት ዘመን

በሐዋርያት ዘመን የአማላጅነት አገልግሎት የተለመደ ነበር። ሐዋርያት በተሰጣቸው የመንፈስ ቅዱ ስ ስጦታ መሠረት በአዲስ አማንያን ራስ ላይ እጅ እየጫኑ (እያኖሩ) መንፈስ ቅዱስን ሲያሰጡና በበሽተኞ ች ላይም እጃቸውን እያኖሩ ሲፈውሱ ያየው ሲሞን ይህን ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን እንዲሰጡት ወ ደ ሐዋርያት ገንዘብ ይዞ ቀረበን እንዲህ አላቸው፤ «እጄን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህን ሥልጣን ስጡኝ።» ጴጥሮስም ይህንን ስምቶ ሲሞንን አጥብቆ ገሰጸው፤ ንስሐም እንዲገባ መከረው። ሲሞን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ (ጸጋ) በገንዘብ መግዛት (መለወጥ) ታላቅ ስሕተት መሆኑን ከተገነ ዘበ በታላ ቅዱስ ጴጥሮስን «ካላችሁን ማለትም ከተናገራችሁት አንዳች እንዳይደርስብኝ እናንተው ወደ ጌ ታ ለምኑልኝ» አላቸው (የሐዋ. 8፥14-25)።

ከዚህ ላይ ከሲሞን አባባል የምንረዳው ዐቢይ ነገር አለ። ይከውም «አንዳች ክፋ ነገር እንዳይደርስብኝ እና ንተው ወደ እግዚአብሔር ለምኑልኝ» ማለት አማልዱኝ ማለቱ በዚያን ጊዜ ሐዋርያት ስለ በደሉ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ይጸልዩና ምልጃንም ያቀርቡ እንደ ነበረ ያረጋግጣል። በአሁኑ ጊዜም ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስ ቲያን ለቅዱሳን አማላጅነት ከፍተኛ ቦታ በመስጠት ወደ እርስዋ በመቅረብና በቅዱሳን ስም በመማጸን ወደ እግዚአብሔር ለምኑልን እያሉ ለሚጠይቁዋት ሁሉ ዘወትር የምልጃ ጸሎት ታደርጋለች። እንደዚሁም ማስታ ረቅም ማማለድ ስለሆነ ማለትም በማማለድ እርቅ እንደሚገኝ የታወቀ ስለሆነ፤ በሰዎች መካከል እርቅና ሰላ ም እንዲሰፍን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ትጸልያለች። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የማስታረቅ አ ገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ መሆኑን አረጋግጦአል (2 ቆሮ. 5፥18)። በተጨማሪም ይህ ቅዱስ ሐዋር ያ ስለ አማላጅነት እንዲህ ሲል አስተምሮናል፤ «እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ፥ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም፤ ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ፥ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ። ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደር ሱ በሚወድ በእግዚአብሄር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነውና» ብሎአል (1 ኛጢም. 2፥1-5።) ስለዚህ ማስታረቅና ማማለድ የቤተ ክርስቲያንና የክርስቲያኖች ሁሉ ተቀዳሚ ግዴታ መሆኑን መ ገንዘብ ያስፈልጋል።

<u>ጥያቄ</u> - የዘመኑ ተከራካሪዎች ክርስቲያኖች በሕይወት ሳሉ ወደ እግዚአብሔር ሊያማልዱና ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቁ ይችላሉ ብለው በዚሁ ረገድ አማላጅነት እንደሚቀበሉ ያረጋግጣሉ። ነገር ግን አጥብቀው የሚከራከሩብና የሚቃወሙት «ሰዎች ከሞቱ በኋላ ሊጸልዩ፣ ልያማልዱ በፍጹም አይችሉ ም» ነው የሚሉትና ለዚህ መልሱ ምንድን ነው?

<u>መልስ</u> - ጻድቃን ወይም ቅዱሳን ሰዎች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው የማማለ ድና የማስታረቅ መብት ከሞቱም በታላ በነፍስ ዓለም ሆነው እንዳያማልዱ የሚከለክላቸው የለም። ስለዚህ ማማለድና መጠለይ ይችላሉ።እስካሁን ከዚህ በላይ የገለጽነው ቅዱሳን (ጻድቃን) በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ማለት ሳይሞቱ ማማለድ እንደሚችሉ ሲሆን፣ከሞቱ በኋላ ደግሞ ማማለድ እንደሚችሉ ቀጥለን እንመለከታለን።

## ቅዱሳን ወይም ጻድቃን በነፍስ ዓለም ሆነው ያማልዳሉ

ቅዱሳን ወይም ጻድቃን ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ በነፍስ ዓለም ማለት በነፍስ አካል ሆነው ማመስገን፣ መጸለይና ማማለድ ይችላሉ። ምክንያቱም በምድር ላይ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው የማማለድ ሥልጣን «በምድር ብቻ እስካላችሁ ድረስ» የሚል ቃል የሌለበት ስለ ሆነ በነፍስ ዓለምም ሆነው በሥጋ ዓለም ላሉ መጸለይ ይችላሉ። ይህንን አስቀድመን፣ መሞት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ቀጥለን እንመለከታለን።

1ኛ. የእግዚአብሔር ወዳጆች ጻድቃን ወይም ቅዱሳን ሞቱ ሲባል ነፍሳቸውም ከሥጋቸው ጋር ወደ መሬት ትመለሳለች፣ ከሥጋቸው ጋርም በመቃብር ወደ አፈር ትመለሳለች ማለት አይደለም። ምክንያቱም የሰው ሁሉ ነፍስ የምትከፈለውና ከሥጋ ጋር የምትዋሐደው በመጀመሪያ ጊዜ ለአዳምና ለልጅ ልጆቹ ከእግዚአብሔር የተሰጠችውና የምትሰጠው ነፍስ ናት። ሰውም ሰው ተብሎ የሚጠራው በነፍሱ ነው። አዳም ሕያው ነፍስ ያለው ፍጡር ሆኖ የቆመው ከእግዚአብሔር በተሰጠችው ነፍስ ነው። «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ» ይላል (ዘፍጥ. 2፥7)።

2ኛ. የሰው ነፍስ ከአፈር የተገኘች ሳትሆን እግዚአብሔር «እምኀበ አልቦ» ማለት ካለመኖር የፈጠራትና ከእግዚአብሔር የተገኘች መሆንዋን መጽሐፍ ቅዱስ ሲመሰክር... «አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይ መለስ፣ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ፣ ፈጣሪህን አስብ» ይላል (መክ. ለ2፥7)። በዚሁ መሠረት መሞት ማለት አንደኛ የሥጋና ለነፍስ መለያየት ማለት ሲሆን ሁለተኛ መሞት ማለት በነፍስ ሕይወት ማለትም በነፍስ አካል ወደ መንፈሳዊው (ወደ የማይታየው ዓለም መሄድ፣ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ማለት ነው። በሞት ጊዜ ነፍስ ወደ እግዚአብሔር እንደምትሄድና ሟቹ ሰው በነፍሱ እግዚአብሔርን ማየት እንደሚችል መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል።

3ኛ. ጻድቁ ኢዮብ በነፍሱ ወደ እግዚአብሔር እንደሚሄድ ሲያስረዳ፣ «ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ፤ እኔ ራሴ አየዋለሁ፤ ዓይኖቼም ይመለከቱታል» ሲል ተናግሮአል (ኢዮብ 19፥26)።

4ኛ. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም መሞት ማለት በነፍስ ወደ ጌታ መሄድና ከጌታ ጋር መኖር ማለት መሆኑን ሲገልጽ፣ ...«ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ሞትም ጥቅም ነውና። ነገር ግን በሥጋ መኖር ለእኔ የሥራ ፍሬ ቢሆንም ምን እንደምመርጥ አላውቅም። በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፤ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና ...» በማለት አስረድቶአል (ፊልጵ. 1፥21-24)።

5ኛ. ነፍሳት በተለይም የጻድቃን ነፍሳት በኢየሩሳሌም ሰማይዊት ከእግዚአብሔር ጋርና ከቅዱሳን መላእክት ጋር እንደሚኖሩ ሐዋርያው ሲያስረዳ፣ ... «ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፤ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፣ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፍ መላእክት፣ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፣ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፣ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች (ነፍሳት) ደረሳችኋል...» በማለት መስክሮአል (ዕብ. 12፥22-24)።

6ኛ. በአካል ነፍስ ያሉትን የቅዱሳንን አማላጅነት የሚክዱ የዘመኑ ተከራካሪዎች ነፍሳት ከሥጋ ከተለዩ በኋላ የት እንዳሉ ማወቅ አይቻልም ይላሉ። እንደዚሁም ነፍሳት ከሥጋቸው ከተለዩ በኋላ ሊጸልዩ ወይም ሊነጋገሩ አይችሉም፣ እያሉ ምእመናንን ያደናግራሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ነፍሳት «ከጌታ ጋር ይኖራሉ፤ ነፍሳት ይጸልያሉ» ይላል። ለምሳሌ ቀጥሎ ባለው ጥቅስ፣ «... አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያው በታች አየሁ። በታላቅ ድምጽም እየጮኩ፣ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፣ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከመቼ አትበቀልም? አሉ። ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፤ እንደ እነርሱም ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቁጥር እስኪፈጸም ድረስ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው» በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል (ራእ. 6፥9-11)።

**ጥያቄ** - ለፍሳትን ከመሠዊያው በታች አየሁ ያለው ምን ማለት ነው?

**መልስ** - *መሠዊያ ማለት መሥዋእት የሚያሳርጉበት ማለት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር መንበር፣ የእግዚአብሔር መቅደስ ሁሉ መሠዊያ ይባላል። በዚሁ መሠረት የእግዚአብሔር ባሪያዎች የነበሩት የሰማዕታት ነፍሳት በግፍ በገደሉአቸው ላይ እግዚአብሔር ፍርድ እንዲፈርድ ሲጸልዩና ሲማልዱ መታየታቸው የቅዱሳን ነፍሳት በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ንስሐ ለሚገቡት ምሕረትንና ሥርየትን፣ ንስሐ በማይገቡት ላይ ግን ፍርድን እግዚአብሔር እንዲሰጥ መለመን እንደሚችሉ ለማስረዳት ነው። ነገር ግን በቅዱሳን ክብር የማያምኑ መናፍቃን ከዚህ በላይ የቀረበውን ማስረጃ እንደማይቀበሉት የታወቀ ነው። «አውቆ የተደበቀ ሲጠሩት አቤት አይልም» እንደሚባለው እነሱ አውቀውና ወደው የቅዱሳንን አማላጅነት ስለ ካዱ ምንም ዓይነት ማስረጃ አይመልሳቸውምና ከእነሱና እነሱን ከመሳሰሉት ጋር መከራከር ጊዜን ማባከን ከመሆኑም በላይ የያዙትንም ንጹህ እምነት ማሳደፍ ነው።* (2ኛ. ጢሞ. 2፥23)።

**አቡነ ገብርኤል በ1990 ካሳተሙት «ክብረ ቅዱሳን» ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ።**